በታላቁ አዳራሽ ውስጥ ደብዳቤውን አቀረብሁላቸው:: ከዚያ ወደ ጽሕፈት ቤታቸው ይዘውኝ ገቡና ስለ አንዳንድ ጉዳዮች ለሩብ ሰዓት እንደተጨዋወትን፥ የጠቅላይ ገዢው ቤተዘመዶችና የተጋበዙ እንግዶች ወደነበሩበት ወደ እንግዳ መቀበያው ክፍል ገባንና ከሁሉም ተዋወቅሁ:: ባለቤቴም ቀደም ብላ ገብታ ከነርሱ ተዋውቃ ነበር:: ከዚያ በኋላ ወደ መብል ክፍል ተዛወርንና ምሳ ተጋበዝን:: ግብዣው እንደተፈጸመ ተሰነባብተን ወደ ሆቴል ተመለስን:: ግንቦት 30 ቀን ወደ ማታ የማሃትማ ጋንዲ አጽም በተቃጠለበት ስፍራ ላይ አበባ አኖርሁ::

የሹመት ደብዳቤዬን ለጠቅላይ ገዢው ካስረከብሁ በኋላ፥ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፕሮቶኮል ሹም ቀጠሮ እየጠየቀልኝ ከሕንድ ሚኒስትሮች ተገናኘሁ:: በኒው ደሊ ለነበሩ የዲፕሎማሲ መልእክተኞች የሹመት ደብዳቤዬን ማቅረቤን ለማስታወቅ ደብዳቤ ከጻፍሁ በኋላም፥ በየተራ ጉብኝቼ ተዋወቅኋቸው:: በአንደኛ ጸሐፊነት እንዲረዳኝ የተመደበው፥ አቶ ወልዴ እንደሻው በካይሮ ሌጋስዮናችን ይሠራ ስለነበረ፥ በቀጥታ ወደ ሕንድ እንደሚሄድ ተነግሮኝ ነበር:: ግን፥ ካሰብሁት ጊዜ በላይ ስለዘገየ፥ ለአያሌ ሳምንቶች ያለ ረዳት መሥራት ግድ ሆነብኝ:: ለሕንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለዲፕሎማሲ ኅብረት የሚጻፉ ደብዳቤዎችን በመኪና እየጻፍሁ መላክ፥ ጸሐፊም ሚኒስትርም ሆኜ ስልክ መመለስና እንግዶችን መቀበል ከሙቀቱ ጋር አድካሚ ነበር:: ለጉብኝትና ለግብዣ ስሄድም፥ ጸሐፊዎች የሉህም ወይ እያሉ ሲጠይቁኝ የምመልሰው ይቸግረኝ ነበር:: ይህን መላልሼ ለንጉሠ ነገሥቱና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማመልከት ጸሐፊው እንዲላክ ተደረገ::

የዲፕሎማሲ መልእክተኛ ሆኜ ወደ ሕንድ እንድሄድ በታዘዝሁ ሰሞን፥ ከአያሌ ዘመናት በፊት በየምክንያቱ ወደ ደቡብ አፍሪቃ ሄደው እዚያ ኑየተራቡትን የሕንድ ተወላጆች፥ ነጮች ባለመሆናቸው ለዘረኛ ፖለቲካው የማይስማሙ ሆነው ስላገኛቸው፥ የነጮች ወገን የሆነው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ከዚያ አገር እንዲባረሩ ለማድረግ መፈለጉ ባያሌው ይወራ ነበር:: አሳቡን በብርቱ በመቃወም፥ የሕንድ መንግሥት በተባበሩት መንግሥታት ዋና ጉባኤ ላይ ጉዳዩ በየጊዜው እየተነሣ ክርክር እንዲደረግበት ያደርግ ነበር:: ንጉሠ ነገሥቱና የኢትዮጵያ መንግሥትም ጉዳዮን ይከታተሉ ስለነበሩ፥ "ሕንዶቹ ከደቡብ አፍሪቃ የተባረሩ እንደሆነ ተከፍለው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ባንዱ ያገር ክፍል እንዲሰፍሩና በሀብታቸው፥ በእውቀታቸው፥ ደማቸውን ከኢትዮጵያውያን ደም በመቀላቀልም፥ ኢትዮጵያን ለማደርጀት እንዲረዱ ቢደረግ፥ ለዘለቄታው የኢትዮጵያ ደኅንነት የሚጠቅም ወይስ የሚጐዳ ይሆን?" የሚል ጥያቄ ተነሥቶ፥ በከፍተኛ ደረጃ ሲመከርበት ሰንብቶ ኖሮ፥ "ወደ ሕንድ መሄዱ ከሆነ እስቲ አማኑኤል የሚለውን እንስማ" በማለት ይመስለኛል፥ ንጉሠ ነገሥቱ አንድ ቀን ጠሩኝና በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየቴን እንዳቀርብ አዘዙኝ:: ሕንዶች በብዛት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲሰፍሩ ማድረግ፥ የሚከተሉት ትውልዶች በቀላሉ ሊላቀቁት የማይችሉት ነቀርሳ ተክለንባቸው ማለፍ መሆኑን ስላመንሁ፥ አሳቡን በመቃወምና ምክንያቴንም በመዘርዘር፥ መጋቢት 9 ቀን 1941 ዓም የተጻፈ ማስታወሻ ለጃንሆይ አቀረብሁ:: ማስታወሻው በሙሉ በዚህ በትዝታ ጽሑፌ ውስጥ ሊገለጽ የሚገባ ስለመሰለኝ፥ እነሆ::

"ከመቶ ዓመት በፊት ጀምሮ፥ በሥራና በንግድ ምክንያት ወደ ደቡብ አፍሪቃ ሄደው ሰፍረው እዚያው የተራቡትን የሕንድ ተወላጆች፥ ነጮች ካለመሆናቸው የተነሣ ለፖለቲካው የማይስማሙ ሆነው በመገኘታቸው፥ ከደቡብ አፍሪቃ እንዲባረሩ የነጮች ወገን የሆነው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ፈልጓል የማለት ወሬ በብዙ ይሰማል:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ፥ እስካሁን ድረስ፥ በሕንድ መንግሥት ጉትጎችነት፥ ጉዳዩ ከማኅበሩ ዋና ጉባኤ ፊት እየተነሣ በየጊዜው ክርክር ይደረግበታል:: በዚህ በመጋቢት ወር መጨረሻ የማኅበሩ ዋና ጉባኤ ኒው ዮርክ ላይ እንደገና ሲሰበሰብም፥ ጉዳዩ እንደገና ሳይነሣ አይቀርም:: ዳሩ ግን፥ የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ይህ የአገር ውስጥ ጉዳይ ስለሆነ፥ የተባበሩት መንግሥታትን አያገባቸውም እያለ ይከራከራል:: ማኅበሩ

ያከረረ እንደሆነም፥ የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ከማኅበሩ ለመውጣት ይገደዳል የሚል ድምፅ ሳያሰማ አልቀረም። በማናቸውም በኩል ሲመለከቱት፥ ይህ ጉዳይ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል።

'የነጮች ወገን የሆነው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ድንገት አሳቡን ከመጨረሻው ማድረስ ችሎ፥ በዚያ አገር ያሉ ሕንዶች እንዲባረሩ የተደረገ እንደሆነ፥ የግርማዊነትዎ መንግሥት ከነዚህ ሕንዶች ተከፍለው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው፥ በአንዱ ክፍል ሰፍረው፥ በሀብታቸውና በእውቀታቸው፥ ደማቸውንም ከኢትዮጵያ ደም በመቀላቀል፥ ኢትዮጵያን ለማደርጀት እንዲረዱ ቢያደርግ፥ ለዘለቄታው የኢትዮጵያ ደኅንነት የሚጠቅም ወይስ የሚጐዳ ይሆን?' ተብሎ ስለተጠየቀው፥ ትሑት አስተያየቴን እንደሚከተለው ለግርማዊነትዎ አቀርባለሁ። የሕንድ ሕዝብ ዓይነቱ ብዙ በመሆኑና በመልክ ቀለም የተለያየ ሆኖ፥ ጥቁረቱ ከሌላው ቀለም አይሎ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የተቃረበ ቢሆንም፥ ከሕንድ ተወላጆች የሚበዙት፥ በተለይም በሰሜንና በሰሜን ምዕራብ ሕንድ የሚኖሩት፥ ከማንም ይልቅ ዝምድናቸው ከኤውሮጳውያን የተቃረበ መሆኑን ታሪክ ያረጋግጣል። እነርሱም 'እንዶ-ዮሮፒያን' ተብለው በኤውሮጳ በሙሉ፥ በፋርስና በሰሜን ሕንድ የሚኖሩትን ሕዝቦች ይጠቀልላሉ። ከዚህም በቀር፥ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በመካከላችን የሚሰፍሩ የደቡብ አፍሪቃ ሕንዶች በአፍሪቃ መሬት ከመቶ ዓመት በላይ መኖራቸው፥ ከነርሱ ይልቅ ጥቃት በሚጸናበት፥ በእውቀት ደረጃም ከሁሉ ባነሰውና፥ በተናቀው የአፍሪቃ ሕዝብ መካከል መቆየታቸው፥ 'አፍሪቃዊ ሁሉ ወራዳ ነው' የሚል ውስጣዊ የንቀት ስሜት ሳያሳድርባቸው የቀረ አይመስለኝም። ለምሳሌ፥ በቅርቡ በደርበን በሕንዶች ላይ የደረሰው ጉዳትና ሞት፥ ምንም እንኳ ቀስቃሹ ኤውሮጳዊ የሆነው ክፍል መሆኑ ቢታወቅ፥ ሕንዶች በአፍሪቃውያን ላይ ካላቸው የንቀት ስሜት የተነሳ፥ አፍሪቃውያኑ ቁጭት ለመወጣት ያደረጉት መሆኑ ጥርጥር የለበትም። ለዚህ መልስ፥ 'ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳ አፍሪቃውያን ናቸው ቢባል፥ በደቡብና በምሥራቅ አፍሪቃ ከሚኖሩ አረማውያን ከሆኑ የአፍሪቃ ተወላጆች ጋር ሊገመቱ አይችሉም፤ ስለዚህ እነዚህ ሕንዶችም ከነርሱ ጋር በአንድ መደብ ላይ ሊያስቀምጡን አይችሉም' ማለት ይቻል ይሆናል። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል፤ ግን አንድ ሰው ሆነ አንድ ሕዝብ፥ በሌሎች ሰዎች ወይም ሕዝቦች አስተያየት መከበርንና መታፈርን የሚያገኘው በእውቀቱ፥ በብልሃቱና በኃይሉ ራሱን የሚችል ሆኖ ሲገኝ ነው።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል በዚህ ግምት የሚታይ ከመቶ ስንት ይሆን? ከደቡብ አፍሪቃ ጀምሮ ምሥራቅ አፍሪቃን በሙሉ ይዞ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ሕንዶች የየሀገሩን ኤኮኖሚ በንግድ ረገድ ማዕከላዊ የሆነ ስፍራ ጨብጠው ስለያዙ፥ ዘመናዊ ዕውቀት የሚጐድለውና፥ ከነርሱ ሊወዳደር የማይችለው ያልታደለ አፍሪቃዊ፥ በኃዘንና በብስጭት መንፈስ እነዚህን ሕንዶች አጥብቆ ይጠላቸዋል። አሁን በግዛቱ ውስጥ ያሉትን ሕንዶች የሚያስጨንቀው ጠንካራ ኃይልና ሥልጣን ያለው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ቢሆንም ፥ የምሥራቅ አፍሪቃ የገዢ ወገኖች የደቡብ አፍሪቃን መንግሥት ደረጃና ኃይል ሲያገኙ፥ በውስጣቸው የሚኖሩትን ሕንዶች እንደዚሁ ሳያስጨንቁ የሚቀሩ አይመስለኝም። ይህም በመላው ዓለም በአይሁድ ላይ ሲደረግ ከኖረው፥ አሁንም ከሚደረገው ጥላቻ ጋር የተመሳሰለ ነው። የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት፥ ከኤውሮጳና ከሌሎች አህጉሮች በየጊዜው የሚሄዱለትን ልዩ ልዩ ወገኖች ከራሱ ልማድ ለማስማማትና ቋንቋውን ለማናገር የቻለው፥ መሠረቱ የማይናወጥ፥ የደረጀና ራሱን የቻለ መንግሥት በመሆኑ ነው። ኢትዮጵያ በተፈጥሮ በተሰጣት፥ በአገርዋ ልምላሜና ሀብት ብዛት የተነሳ፥ አሁን ካለው ሕዝብዋ ሦስትና አራት እጥፍ የሚሆን ለማኖር ትችላለች። ትምህርት ቢስፋፋና ልጆችዋ ሁሉ ማን መሆናቸውን አውቀው፥ ያሉበትን ደረጃ ተገንዝበውና ተባብረው ቢሠሩ ኖሮ፥ ኢትዮጵያ ካላት የሀገር ስፋት መጠን አንፃር ሲተያይ፥ ሀብታሞች ከሚባሉት እንደ አርጀንቲና፥ እንደ ሜክሲኮ፥ እንደ ቱርክ ካሉት አገሮች ልትተካከልና በዓለም መንግሥታት ፊት መከበርንና መታፈርን ለማግኘት በቻለች ነበር። በዚህ አኳኋን 'የሕንዶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ኢትዮጵያን ከዚህ

2

ግብ ለመድረስ ይረዳታል ወይስ አይረዳትም' ተብሎ ቢጠየቅ፥ በእኔ ትሑት አስተያየት በአሁኑ የኢትዮጵያና የሕንድ አኳኋን 'አይረዳትም' ነው የምለው:: ዋና ዋናዎቹን ምክንያቶች እንደሚከተለው እገልፃለሁ::

1. ሕንዶች ከጥንት ጀምሮ በዘር በጣም የተለያዩ ሕዝቦች ናቸው:: ቆዳቸው እጅግ የነጣና እጅግ የጠቆረ ሰዎች አሉባቸው:: በስተሰሜን በካሽሚር የሚኖሩት፥ ንጣታቸው እንደ ስዊዲኖች ነው ይባላል:: በስተደቡብ የሚኖሩትም ጥቁረታቸው፥ ከአፍሪቃ ሻንቅሎች ምንም ያህል የሚያንስ አይደለም:: የእንግሊዝ መንግሥት አንድ መቶ ሃምሳ ዓመት ያህል፥ አንድነት ጨፍልቆ በበረታ ክንድ ባይገዛቸው ኖሮ፥ ሕንድ ወደሁለት መንግሥት ብቻ ሳይሆን፥ ምናልባት ወደሀያ መንግሥት በተከፋፈለች ነበር:: ካንዱ የሕንድ ክፍል ወደ ሌላ ክፍል የሚሄድ ሕንዳዊ፥ በቋንቋ፥ በልማድ፥ ብዙ ጊዜም በሃይማኖትና፥ "ካስት' በተባለውም የኑሮ ደረጃ ልዩነት የተለየየ ከመሆኑ የተነሣ፥ ከሌላ ልዩ አገር እንደመጣ እንግዳ ሰው ያህል ነው ባይተዋር የሚሆነው:: የእንግሊዝ የጭቆና አገዛዝና የትምህርት መስፋፋት፥ ሕንዶችን አንድ ሕዝብ አድርጓቸዋል:: ይልቁንም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ሕንዶችን ከቀድሞው ይልቅ አሳብ ለአሳብ እንዲገናኙ ለማድረግ እጅግ ረድቷቸዋል::

እስካሁን ድረስ እንደታየውም፥ ሕንዶች ምንም እንኳ በብዙ አገሮች ውስጥ ተሰራጭተው ቢኖሩ በጋብቻ፥ በልማድም ሆነ፥ በሃይማኖት ከሚኖሩባቸው ሕዝቦች ጋራ እንዳይቀላቀሉ በጣም ይጠነቀቃሉ:: ለምሳሌ፥ የሕንድ ጐረቤቶች በሆኑ እንደ በርማ፥ ሲሎንና ማሌሺያ ባሉት አገሮች፥ ብዙ ሕንዶች ከብዙ ዘመን ጀምሮ ይኖራሉ:: ዳሩ ግን፥ እነዚህ ሕንዶች ካገሩ ሰዎች ጋር አልተቀላቀሉም:: እነዚህ አገሮች እንደ ሕንድ ባንድ የእንግሊዝ መንግሥት ይገዙ በነበረ ጊዜ ችግሩ ጐልቶ አልታየም ነበር:: አሁን ግን በርማና ሲሎን እንደ ሕንድ ነፃነትን ካገኙ ወዲህ አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ተነስቷል:: እንደሰማሁት፥ የበርማ መንግሥት ከሁለት ዓመት ወዲህ፥ ቀድሞ በዚያ አገር ርስት ተተክለው የነበሩትን ሕንዶች ነቅሎ መሬቱን ለበርማ ሕዝብ ለመመለስ ፈልጓል:: የሕንድ መንግሥትም በበኩሉ፥ ይህ እንዳይደረግ አጥብቆ ይከራከራል፤ እስካሁን ድረስ ሁለቱ መንግሥታት መስማሚያ መንገድ በመፈለግ ላይ ናቸው:: በሲሎንም ብዙ ሕንዶች ከብዙ ትውልዶች በፊት ጀምሮ ስለሚኖሩ፤ አሁን ሲሎን ነፃነት ስታገኝ፥ የሲሎን ዜጎች እንዲሆኑ፥ አለዚያም አገራቱን ለቅቀው ወደ ሕንድ እንዲመለሱ ስላስገደደች፥ የሚበዙት ባለርስቶችና ባለጸጎች ከመሆናቸው የተነሣና፥ በሕንድ የተሻለ ኑሮ ማግኘት የማይችሉ መሆናቸውን ስለተገነዘቡ፥ የሲሎን ዜጎች ሆነዋል:: ግን ለእኔ እንደሚመስለኝ፥ ይህን ያደረጉት የጊዜውን ችግር ለመወጣት እንጂ፥ የሚኰሩባት አገራቸውንና ጥንታዊ ታሪካቸውን ለዘለቄታው ለመተው በማሰብ 'አይደለም::

እንግዲህ ሕንዶች በዘር፥ በልማድ፥ በሃይማኖትም ከሚመስሏቸው የበርማና የሲሎን ሕዝቦች መዋሐድ ያልሆነላቸው፥ ወደ አፍሪቃ ተሻግረው በኢትዮጵያ ቢኖሩ ዘራቸውን፥ ልማዳቸውን፥ ዜግነታቸውንና ሃይማኖታቸውን ረስተው፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ተቀላቅለው፥ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን ሊሆኑ ይችሉ ይሆን? እኔ ያጠራጥረኛል::

2. በሃይማኖትና በአስተያየት ረገድ፥ የሕንድ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የራቀ መስሎ ይታየኛል:: የምሥራቅ ሕዝቦች በመሆናቸው፥ ሁለቱም በመንፈሳዊ ጉዳይ ብርቱ ናቸው ለማለት ቢቻልም፥ የሕንድ ሕዝብ መንፈሳዊነት ምንም እንኳ በኛ የክርስቲያን አስተያየት የተሳሳተ መስሎ ቢታይ፥ እጅግ ጥልቅ ከመሆኑ የተነሣ፥ በአሁኑ አኳኋን የኢትዮጵያ ሕዝብ

ሊያስትውለው የሚሻ፥ የሚችልም አይመስለኝም። ሕንዶችም፥ በመሳሳትም ቢሆን በእውቀት፥ ልዩ አስተያየት ስላላቸው በቀላል ወደ ክርስትና የሚገቡ አይመስለኝም። ይህ ሲሆንና በመካከላችን ያለው የእስላም ሃይማኖት ብርቱ ስጋት ሲያሳድርብን፥ ከዚያ የረቀቀው የሕንድ ሃይማኖት በመካከላችን ስር የሰደደ እንደሆነ ለክርስቲያን ሃይማኖታችን፥ በመጨረሻም ለአንድነታችን እጅግ አስጊ ነገር ይሆናል። ከሚመጡት ሕንዳውያን የሚበዙት እስላሞች የሆኑ እንደሆነም፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የሃይማኖት ወንድሞቻቸው በእውቀት የሚበልጡና፥ ሕንድን ራሷን ለሁለት ለመክፈል መሣሪያ ከሆኑት ወገን ስለሚሆኑ፥ ለኢትዮጵያ ሕይወትና አንድነት የበለጠ የሚያስፈራ ነው።

3. ሕንድ ለሁለት መቶ ዓመት ያህል መንግሥቷ ጠፍቶ፥ በባዕድ ተቀጥቅጣ ተገዝታ፥ አሁን በታላቅ ተጋድሎ በገዛ ልጇ የሚተዳደር መንግሥት ስላቆመች፥ ለመላው የሕንድ ዘር ታላቅ ደስታና ኩራት የሚሰጥ ሆኗል። ከነርሱም አልፎ ለመላው የጥቁር ዘር ታላቅ የደስታና የተስፋ ምንጭ ሆኗል። በዚህ አኳኋን፥ ምንም ቢቸገሩ፥ ሕንዶችን አገራችሁንና መንግሥታችሁን ትታችሁ ወደ ኢትዮጵያ መጥታችሁ፥ ዜግነታችሁን ለውጣችሁ፥ ገንዘባችሁን፥ እውቀታችሁንና ደማችሁንም ከኛ ጋር በመቀላቀል ኢትዮጵያን እርዱ ቢባሉ፥ ቅር የሚላቸው ይመስለኛል። እንደ እኔ አስተያየት፥ ሕንዶች ብዙ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ቢኖሩ ደስ ይላቸዋል። ይህን የሚፈልጉት ግን፥ ዜግነታቸውና ሃይማኖታቸው ሳይለወጥ፥ ደማቸው ሳይቀላቀል መኖር የቻሉና፥ ሲያሰኛቸው ወደ ትውልድ አገራቸው መመለስ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲፈልጉ ወደ ኢትዮጵያ እንደልባቸው እንዲገቡ የሚፈቀድላቸው እንደሆነ ብቻ ነው። የዚህ ዓይነት ኑሮ ግን ለኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ የሚመጥን፥ ኢትዮጵያንም የሚያስከብር አይሆንም። ይልቁንም፥ የኢትዮጵያ ዘር የትምህርት ደረጃ ከሚመጡት ሕንዶች የትምህርት ደረጃ ዝቅ ያለ እንደሆነ፤ የኢትዮጵያን የኤኮኖሚ ሕይወት በእጃቸው ጨብጠው የሕዝባችንን ጉልበት በጥቂት ዋጋ በመግዛት ከውርደት እንዳይጥሉንና እንዳያደኸዩን የሚያሰጋ ይሆን ይመስለኛል። ይህም፥ ኢጣልያ ከተመኘችልን ምንም ያህል የሚሻል አይሆንም።

4. ከላይ እንደጠቀስሁት፥ በደቡብና በምሥራቅ አፍሪቃ ከኤውሮጳውያን የተረፈው የአገሩ ሀብት የሚበዛው በሕንዶች እጅ ስለሆነ፥ የአፍሪቃ ተወላጅ የሆነው ሕዝብ ከመጠን በላይ በድህነት ተጐሳቁሎ ይታያል። ምቹ ጊዜና አኳኋን ቢያገኝም፥ ሕንዶችን አርዶ ቢዘርፋቸው አይጠላም። እንደምሰማው፥ በኤውሮጳ ሰው ቂም ከሚይዝ በሕንድ ሰው ቂም መያዝ ለአንድ አፍሪቃዊ የቀለለ ነገር ነው። ምክንያቱም፥ በየዕለቱ ሕይወቱን በሚነካ ነገር ሁሉ የሚገናኘው ከሕንድ ነጋዴና ሸቀጥ ሻጭ ስለሆነ ነው። ከክብሪት ጀምሮ እስከሚለብሰው ጨርቅ ድረስ አፍሪቃዊው የሚገዛው ከሕንድ ሰው ነው። ከዚህም በቀር፥ ከኤውሮጳውያን የሚተርፈውም ማንኛውም የቢሮ ወይም ሌላ ጥቂት እውቀትን የሚያሻው ሥራ የሚያዘው በሕንድ ተወላጅ ሆኗል። ማንኛውም ሕንድ ደግሞ በበኩሉ አፍሪቃዊውን ይጸየፈዋል። ይህ የሚያፋቅር ነገር ሊሆን አይችልም። በሌላ አፍሪቃ ሀገሮች እንግዲህ ሁኔታው እንደዚህ ነው። ታዲያ. ሕንዶች ኢትዮጵያ መጥተው የኢትዮጵያዊነት መብት ቢሰጣቸው እንዴት ያደርጉ ይሆን? መንግሥቱን የሚመሩት ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ፥ ለጊዜው በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዳያይሉ ይታገዱ ይሆናል። ግን፥ እነርሱም ዜጎች ከሆኑና የዜጋን መብትና ነፃነት ካገኙ፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሹመትና ሌላም በር ሊከፈትላቸው ግድ ይሆናል። በአሁኑ አኳኋናችን እንደሚገባ ከእነርሱ መወዳደር የሚቻለን አይመስለኝም። በእኔ አስተያየት፥ ነጮቹ የደቡብ አፍሪቃ ሰዎችም ሊያስወጡአቸው የሚመኙበት ዓይነተኛው

4

ምክንያት ይህንኑ ውድድር ስለፈሩ ነው። ነጩ ሁሉ ወደ ትምህርት ቤት በሚሄድበት በደቡብ አፍሪቃ ያን ያህል የሚያሰጉ ከሆነ፥ ከሺህ ሕፃናት መካከል ሦስት ብቻ ወደ ትምህርት ቤት በሚሄድበት በዛሬይቷ ኢትዮጵያ የቱን ያህል ያሰጉ ይሆን?

<u>ግርማዊ ሆይ!</u> ከላይ የተዘረዘረው ሁሉ በፍርሃት ላይ የተመሠረተ ይመስላል። የእኔ ፍርሃት ግን፥ አንድ ኢትዮጵያዊ እኩል መብትና እኩል እውቀት ቢያገኝ ከማናቸውም የውጭ አገር ሰው ያንሳል በማለት አይደለም። ዳሩ ግን፥ በዚህ ባሁኑ ዘመን ከማናቸውም ነገር ይልቅ እውቀትና ብልሃት ገነው ስለሚታዩ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብዎ በግርማዊነትዎ ሰፊ አስተያየት ያንን ዘመናዊ እውቀትና ብልሃት ገንዘቡ ማድረግ ጀምሯል። ይህም ስለተባለ፥ በዘመናዊ እውቀት የገፉ አምስት ሺህ እንኳ የሚያህሉ የውጭ ሰዎች መጥተው በአገራችን ውስጥ ቢተከሉ፥ በማንኛውም ረገድ ከነርሱ ሊወዳደሩና እነርሱ ሊሠሩ የሚችሉትን የሚሠሩ አምስት ሺህ ኢትዮጵያውያን መኖራቸው ያጠራጥረኛል። ከዚህ የተነሣም፥ ይህ በዘመናዊ ዕውቀት ገና ሕፃን የሆነ ሕዝብዎ፥ ከጉዳት ላይ እንዳይወድቅና መንግሥቱ እንዳይናወጥ፤ ንግድ ወይም እንዱስትሪ በ 'ታሪፍ' እንደሚጠበቅ የሕንዶችም ሆነ የሌሎች የውጭ ሰዎች አገር ገብቶ መስፈር በጥንቃቄ ሊጠበቅ የሚገባ ይመስለኛል።

ይሁን እንጂ፥ በእኔ ትሑት አስተያየት፥ ይህ ጥበቃ አፍራሽ (<u>'ነጋቲፍ</u>) ይዘት ብቻ ያለው እንዳይሆን በጣም መጠንቀቅ ያሻል። ይህም ማለት፥ ከውጭ ጉዳት የሚያመጣውን እንዲያው በቀላሉ መከላከል ብቻ ሳይሆን፥ ሕዝቡ ራሱን ችሎ እንዲቆምና በራሱ በመተማመን ከሌሎች ጋራ መወዳደር የሚችልበትን መሣሪያ በተቻለ ፍጥነት ማቀበል ነው። ያም መሣሪያ፥ ግርማዊነትዎ ከብዙ ዘመን አስቀድሞ የተገነዘበው የትምህርትና የእውቀት በሕዝብዎ መካከል እንዲስፋፋ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያን በሁሉም ረገድ በእውነት ነፃ የሆነች፥ በጓደኞችዋ ፊት የታፈረችና የተከበረች አገርና መንግሥት ሊያደርጋት የሚችል የትምህርት መስፋፋት ብቻ ነው። ስለዚህ፥ ግርማዊነትዎ የጣለው መልካሙ የትምህርት መሠረት ተስፋፍቶና ደርጅቶ ከፍጻሜ ደርሶ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ በተቻለ ፍጥነት ከሌሎቹ ሕዝቦች ጋራ እንደሚያስተካክላቸው ጽኑ ምኞቴና ተስፋዬ ነው" የደቡብ አፍሪቃም መንግሥት ሕንዶችን ከአገሩ በማስወጣቱ አሳብ ላይ ብዙ አልገፋበትም። ንጉሠ ነገሥቱም፥ ሕንዶችን ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ ስለ ማስፈር ጉዳይ፥ መጋቢት 9 ቀን 1942 ዓም እንደሚከተለው ጻፉልኝ፤ ... የሕንድ ሰዎች ወዳገራችን እንዲገቡና ሕዝባችን እንዲበዛ ለማድረግ ባሰብን ጊዜ የጻፍከውን ማስታወሻ ተመልክተን፥ ሃሳብህ መልካም በመሆኑ የሕንድ ሰዎች በብዙ ወደዚህ መግባታቸው እንዲቆይ ተደርጓአል።"

ወደ ሕንድ ከሄድሁ ከሁለት ዓመት ያህል በኋላ ግን፥ መጋቢት 22 ቀን 1943 ዓም፥ ንጉሠ ነገሥቱ እንደገና የሚከተለውን ጻፉልኝ። "በአፍሪቃ ስላሉት ሕንዲዎች ሁለተኛ ያነሣንብህ፥ በፕሪንስ ዓሊካን አስታዋሽነት፥ በእስላም ሃይማኖት የሚያምኑት ተመርጠው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ መታሰቡንና እስላሞች ብቻ ሳይሆን፥ የሕንድ ሃይማኖትን የሚከተሉትም እንደዚሁ ተመርጠው የግብርናና የከብት ርቢ ሥራ ለመሥራት የሚፈቅዱት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እንዲሰፍሩና፥ የተወሰነ ዘመን ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያን ዜግነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ስለታሰበ፥ በኦፊስዬልም ባይሆን፥ ከሕንድ ባለሥልጣኖች ጋራ ተነጋግረህበት የሃሳባቸውን መሠረት ብናውቀውና ጥቂት የተመረጡ ሕንዲዎች ለመቀበል አስበንበታልና ጉዳዩን እንድትከታተለው።"

እኔም፥ ወደ ሕንድ ከመሄዴ በፊት ያቀረብሁትን ማስታወሻ በመጥቀስና ከዚያም በኋላ ለሁለት ዓመት ያህል በሕንድ በመኖር እንደተመለከትሁት፥ በሕንድ ጐረቤት አገሮች የሚኖሩ ሕንዶች ለነዚያ አገሮችና ለሕንድ የወዳጅነትና የመጠቃቀም ምክንያት በመሆን ፈንታ፥ ግንኙነታቸውን የሚያሻክር ጠንቅ መሆናቸውን

በመግለጽ ሚያዝያ 8 ቀን 1943 ዓም አንድ ማስታወሻ ለጃንሆይ ላክሁ:: ማስታወሻውም የሚከተለው ነው::

"ግርማዊ ሆይ! በፐሪንስ ዓሊካን አስታዋሽነት፥ በአፍሪቃ ካሉ ሕንዶች በእስላም ሃይማኖት የሚያምኑት ተመርጠው ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ መታሰቡንና እስላሞቹን ብቻ ሳይሆን፥ የሕንድን ሃይማኖት ከሚከተሉትም እንደዚሁ ተመርጠው የግብርናና የከብት ርቢ ለመሥራት የሚፈቅዱት ወደ ኢትዮጵያ ሄደው እንዲሰፍሩና የተወሰነ ዘመን ከቆዩ በኋላ የኢትዮጵያን ዜግነት እንዲቀበሉ ለማድረግ ስለመታሰቡ ከሕንድ ባለሥልጣኖች ጋራ እንድነጋገር መጋቢት 22 ቀን የተጻፈው የግርማዊነትዎ ትእዛዝ ደርሶልኛል:: እንደ ጃንሆይ ትእዛዝ ፈጽሜ በቅርቡ የባለሥልጣኖቹን አስተያየት ለግርማዊነትዎ እንዳቀርብ ተስፋ አለኝ:: ይህን ከማድረጌ አስቀድሞ ግን፥ ኢትዮጵያ የምትቀበለው አሁን በአፍሪቃ የሚገኙትን ሕንዶች ብቻ ነው ወይስ ከዚህ ከሕንድም ለመሄድ የሚፈቅዱትንም ይጨምራል? የዚህ ጥያቄ መልስ እንዲላክልኝና እንዳውቀው እለምናለሁ::

ወደ ሕንድ እንድመጣ በታዘዝሁ ጊዜ ከአዲስ አበባ ሳልነሣ፥ ስለዚህ ጉዳይ አሳቤን እንዳቀርብ ግርማዊነትዎ አዝዞኝ፥ መጋቢት 9 ቀን 1941 ዓም ለጃንሆይ ባቀረብሁት ማስታወሻ፥ በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ ብዙ ሕንዶች ሄደው በአገራችን ቢሰፍሩ ከጥቂት ዘመን በኋላ እንዴት ያለ ጉዳት ለማምጣት እንደሚችል የተቻለኝን ያህል ዘርዝሬ አቅርቤ ስለነበረ አሁን አልደግመውም:: ነገር ግን፥ ይህን ምክንያት በማድረግ ለግርማዊነትዎ ለማመልከት የምደፍረው፥ ከሁለት ዓመት በፊት አዲስ አበባ ላይ ሆኜ ስለዚህ ጉዳይ የጻፍሁትን ማስታወሻ መልሼ ሳነበውና ከዚያ ወዲህ በአገሩ ውስጥ ከመኖሬ የተነሣ፥ በደቡብ አፍሪቃ ብቻ ሳይሆን፥ የሕንድ ጐረቤቶች በሆኑ እንደ ሲሎን፥ በርማና ማሌያ ባሉ የእስያ አገሮች የሚኖሩት ሕንዶች፥ ከሚኖሩባቸው አገሮች ሕዝቦች ለመዋሃድ ካለመፍቀዳቸው የተነሣ፥ በሕንድ መንግሥትና በጐረቤቶቹ መንግሥቶች መካከል ብዙ ችግር ማምጣታቸውን፤ የነርሱ በነዚያ አገሮች መኖርም ለሕንድና ለጐረቤቶቿ የወዳጅነትና የመጠቃቀም ምንጭ በመሆን ፈንታ፥ ፍቅራቸውን እየመረዘ የሚሄድ መስሎ መታየቱን ከቀድሞው ይልቅ አሁን የበለጠ መገንዘቤን በትሕትና እገልጻለሁ::

ለምሳሌ፥ በሲሎን አንድ ሚልዮን የሕንድ ተወላጆች አሉ:: ከነርሱም ብዙዎቹ ከአያሌ ትውልድ በፊት ጀምሮ አባቶቻቸው በዚያ አገር የሰፈሩ ናቸው:: ሲሎን ነፃነትዋን ካስመለሰች ወዲህ፥ "በዚህ አገር የሚኖሩ ሕንዶች ሁሉ የሲሎን ዜጎች ይሁኑ:: ይህን የማይፈቅዱ የሆነ እንደሆነም፥ የዜጋን መብት አያገኙ:: ወደፊትም ሕንዶች እንደቀድሞ ወደ ሲሎን በብዙ ከመፍለስ ይታገዱ" የሚል በሕግ መንግሥቷ ውስጥ ስለተደነገገ፥ ከሕንዶች ጥቂቶቹ በሕጉ መሠረት የሲሎንን ዜግነት ሲቀበሉ፥ የሚበዙት የሕንድን ዜግነት መልቀቅ ስላልፈቀዱ፥ ዜግነታቸውን እንደያዙ በሲሎን እንዲቀመጡና እንደቀድሞው እንዲጠቀሙ እንዲረዳቸው በየጊዜው ወደ ሕንድ መንግሥት ይጮሃሉ:: የሕንድ መሪዎችም "የምትኖሩበትን አገር ዜግነት ተቀብላችሁ ብትኖሩ የተሻለ ነው" እያሉ ቢመክሯቸውም፥ ሰዎቹ እሺ ያሉ መስሎ አይታይም:: ከዚህ የተነሣ፥ የሕንድ መንግሥትና የሲሎን መንግሥት የሚያደርጉት ቸግሯቸዋል:: የወዳጅነት ግንኙነታቸውም ብዙ እንዳይመረዝ ለማድረግ ይጥራሉ:: የጉዳዩን አስቸጋሪነትም የሁለቱ አገሮች መሪዎች በየጊዜው እንዳነሡ ናቸው:: በበርማና በማሌያም ጉዳዩ ገና አልተጋጋለም እንጂ፥ እንደዚሁ ያለ ችግር መኖሩ ከማንም የተሰወረ አይደለም:: በበርማ ያሉ የሕንድ ተወላጆች ቁጥር 600 ሺህ ያህል ነው ይላሉ::

በደቡብ አፍሪቃ፥ የማላን መንግሥት በዘር ልዩነት እያስመሰለ በአፍሪቃውያንና በቀለም ሰዎች ላይ ሁሉ ያወጣው ሕግ ምንም እንኳ እጅግ የሚያሳዝን ቢሆን፥ በደቡብ አፍሪቃ፥ ገዢው ወገን የነጭ ዘር ስለሆነና ካሁን በፊት አያሌ መቶ ዘመን ጥቁሮችን እንደልቡ ስለገዛ፥ ምክንያት ያገኘ መስሎት በዘር ልዩነት አመካኝ እንጂ፥ በጥልቅ አስተያየት ሲመለከቱት፥ የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ነጭ

6

ያልሆነውን፥ በአገሩ የሚኖረውን የሰው ዘር ለማጥቃትና ለማዋረድ ታጥቆ የተነሣበት ዓይነተኛው ምክንያት፥ በኤኮኖሚና በኑሮ ረገድ በሁለቱ ወገኖች መካከል ትክክለኛነትና የመብት እኩልነት እንዳይኖር ነው። በአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ ነጩ ወገን ጥቁሩን የሚገፋና የሚያጠቃም፥ ስሙ በዘርና በመልክ ቀለም ልዩነት ነው ይባል እንጂ፥ ሁለቱን ወገኖች የሚያጣላው እውነተኛው ነገር ነጩ ወገን ጌትነቱን መልቀቅ ስለማይፈቅድና ጥቁሮች እኩልነትን በማግኘታቸው የጥቁርን ጉልበት በጥቂት ዋጋ ማግዛቱ የቀረበት እንደሆነ፥ የኑሮው ደረጃ ካሁኑ ዝቅ የሚልበት ስለሚመስለው ነው። የነጭ ወገን ነው የማይባለው የሲሎን መንግሥትም፥ በአገሩ ላሉት ሕንዶች በተለይ ዜግነቱን አንቀበል ላሉት፥ የዜጋ መብት ላለመስጠት ለመቁረጡና ከአገሩ ለማስወጣት ለመፈለጉ እውነተኛው ምክንያት የሕንዶችን ውድድር ስለፈራ፥ ዜጎቹ ያልሆኑ ሕንዶች በአገሩ ውስጥ የበረከቱ እንደሆነ፥ ለኤኮኖሚ ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን፥ ለፖለቲካ ነፃነቱም የሚያሰጋው መሆኑን በመገንዘቡ ነው።

አሁን ለጊዜው በያለበት የነጭና የጥቁር ትግል መስሎ የሚታየው ይህ አኳኋን፥ ቀድሞ የሶስያሊስት መንፈስና አስተያየት በመላው ዓለም በሰፊው ሳይሰበክ ተስፋፍቶ የነበረ፥ አሁንም ቢሆን በያገሩ የሚታይ፥ በታሪክ እጅግ ጎልተው የሚታዩትን የፈረንሳይንና የመስኮብን ረቮሉስዮኖች ያፈራ፥ የኤኮኖሚና የፖለቲካ ነፃነቱን ለማረጋገጥና ከኃይለኞች ጥቃት ለመዳን፥ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ያደረገው፥ አሁንም የሚያደርገው፥ የማያቋርጥ ተጋድሎ ነው። በዚህ አኳኋን፥ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አሁን የሚታሰበውን ጉዳይ ከመጨረሻው አድርሶ፥ ብዙ ሕንዶች በኢትዮጵያ ምድር የተተከሉ እንደሆነ፤ ለሚከተሉት ለኢትዮጵያ ትውልዶች ብርቱ ጠንቅና መሰናክል ትቶ ከማለፍ በቀር፤ የሕንድ ጐረቤቶች በሆኑት አገሮችና በአፍሪቃ ክፍሎች እንደሚታየው፥ በችግር ጊዜ ወዳጅና ጓድ እንዲሆነው ከሚመኘው ከሕንድ መንግሥት ጋር የሚያቀያይመው መሆኑን እንደማምን በታላቅ ትሕትና ለግርማዊነትዎ ሳመለክት፥ የኢትዮጵያዊነት ስሜቴንና የአገልጋይነት ተግባሬን ለመግለጽ እንጂ፥ ለድፍረት ወይም በተለይ ሕንዶችን የመጥላት መንፈስ ስላለኝ አለመሆኑን ግርማዊነትዎ እንዲያምን እለምናለሁ። አሁን የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ከአገሩ ሊያስወጣቸው ወይም የሰው ልጅነትን መደብ ሊነሣቸው የሚታገለውን ሕንዶች፥ የጊዜውን ጥቅም እንጂ ኋላ የሚከተለውን አርቆ ባለመመልከት ወደ አፍሪቃ የወሰዱ፥ ከማላን በፊት የነበሩ በየጊዜው የተሾሙ የዚያው አገር ባለሥልጣኖች እንደነበሩ አለመዘንጋት እጅግ የሚጠቅም ይመስለኛል።"

ይህን ማስታወሻ ለንጉሠ ነገሥቱ ከላክሁ በኋላ፥ ሕንዶችን በኢትዮጵያ የማስፈር ጉዳይ ስላልተነሣና ከሕንድ ባለሥልጣኖች ጋር ስለጉዳዩ ሳልነጋገር ወደ አገሬ ስለተመለስሁ በጣም ደስ አለኝ። ከላይ የተመለከቱት ሁለት ማስታወሻዎች አገሬን ከብርቱ የፖለቲካና የኤኮኖሚ ጠንቅ ለማዳን እንደረዱ በማመን ልዑል አምላኬን አመሰግናለሁ። ይህ በሚያዝያ 1943 ዓም የሰነዘርሁት ሐሳብ፥ የሕይወቴን ትዝታ መጻፍ በጀመርሁበት፥ በሚያዝያ 1977 ዓም እውነተኛ ሆኖ መገኘቱና ከአያሌ ትውልድ በፊት በሰሜን ሲሎን (ዛሬ ስሪ ላንካ) የሰፈረው፥ ታሚል የተባለው የሕንድ ወገን ሕዝብ፥ በስሪ ላንካ ምድር የራሱን መንግሥት ለማቋቋም በመሻት፥ የጦር መሣሪያ አንሥቶ የስሪ ላንካን ሕዝብ ሲያደማ መመልከት አንዳችም ደስታ የሚሰጠኝ ባይሆንም፥ ንጉሠ ነገሥቱ ማስጠንቀቂያዬን ተቀብለው፥ በዚያ ዘመን ታስቦ እንደነበረው፥ ሕንዶች በኢትዮጵያ እንዲሰፍሩ ሳያደርጉ መቅረታቸው በይፋ ሲገለጽ፥ በኢትዮጵያ ተከታታይ ትውልዶች ዘንድ የሚያስመሰግናቸው እንደሚሆን እተማመናለሁ።

በሕንድ አገር በኖርሁበት ዘመን፥ በአገሩ የውስጥ አስተዳደር፥ በፖለቲካ፥ በኤኮኖሚና በማኅበራዊ ኑሮ ጉዳዮች ላይ፤ እንደዚሁም በሕንድ ጐረቤት አገሮች ሁኔታና በሕንድና በነዚያ አገሮች መካከል በነበረው የወዳጅነት ወይም የጠላትነት ግንኙነትም ላይ አያሌ ማስታወሻዎችን ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርቤ ነበር። ~~ለዚሁም~~

7